ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ–ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 46 ሀምሌ 30/2018 ዓ.ም


## በውስጥ ገጾች

ተስፋን እንትከል በሚል መሪ ቃል የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች የችግኝ ተከላ አካሄዱ
ገጽ 2

ኮሚሽኑ በቀጣይ አዎንንታዊ ሙስናን የመከላከል ስትራቴጂ በመከተል ይሰራል - ኮሚሽነር ማሞ ቴጋ
ገጽ 3

የሀገር ሀብትና የዜጎች መብት ጥበቃ በቴክኖሎጂ የተደገፈው የፀረ-ሙስና ትግል
ገጽ 6


**የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካለዎት NCRS ሞባይል መተግበሪያ ባሉበት ሁነው ይጠቁሙ!**

## የኢትዮጵ ህዝብ ሌብነት በቃኝ ብሏል - ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)



ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በወቅታዊ ጉዳይ ላይ ከአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን ጋር ቆይታ ማድረጋቸው ይታወቃል: ፡ በዚህ ወቅት እንደተናገሩት የኢትዮጵ ህዝብ ሌብነት በቃኝ፤ ሌቦችን ከውስጣችሁ አጥሩ፤ ሌብነት የተንሰራፋበት ብልጽግና አልትሜት ውጤት አያመጣም ብሏል። ቀን ከሌት የማይሰሩ፣ የማይተጉ እና ስልጣን ወንበር መጠበቂያ አድርገው የሚያስቡ እንዲሁም በተጨባጭ ውጤት ማያመጡ ሰዎችን ፈትሹ ብሏል ሲሉ በአፅንኦት ተናግረዋል።

## 4ኛው አገራዊ የሙስና ጥናት ይፋ ሆነ

በኢትዮጵያ በ12 ክልሎች እና በሁለት የከተማ አስተዳደሮች በምሁራን የተካሄደው 4ኛው አገራዊ የሙስና እና የተጋላጭነት ጥናት፣ እንዲሁም ተቋማዊ የግምገማ ሪፖርቶች ይፋ ሁኗል። ጥናቱ በከተሞችና በገጠር አካባቢዎች ሙስና አሁንም አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ያመለከተ ሲሆን፣ በተለይም በመሬት አስተዳደር፣ በግዥ አሰራር፣ በበጀት እና በመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ላይ ከፍተኛ የተጋላጭነት ደረጃ መኖሩን ይፋ አድርጓል።





በምሁራን በቀረበው የጥናት ሪፖርት መሠረት የመሬት አስተዳደር፣ የቀበሌ አገልግሎቶች፣ የንግድ ፈቃድ አሰጣጥ፣ የበጀት

ወደ ገጽ 2 የዞረ

## በሙስናና ሕገ-ወጥ አሠራር የተሳተፉ አካላት ላይ የሕግ እርምጃ ተወሰደ

በኢትዮጵያ ተግባራዊ እየተደረገ ያለውን ሰፊ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ለማደናቀፍ በሚንቀሳቀሱ እና የሀገር ሀብት በሚመዘብሩ አካላት ላይ መንግሥት የማያዳግም እርምጃ እየወሰደ መሆኑን አስታወቀ።
የኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ወይዘሮ እናትዓለም መለሰ ዛሬ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፤ ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት ፈጣን ልማትና ዕድገት እንድታረጋግጥ በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቅሰው፣ በዚህም ሰፋፊና አስደናቂ ሀገራዊ ውጤቶች



መመዝገባቸውን ገልጸዋል።
በዚህ ሂደት ግን ይህ ውጤት ጉዞው አልጋ በአልጋ እንዳልነበር አመላክተዋል። ከተለያዩ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ተግዳሮቶች ባሻገር፣ ሕገ-ወጥነት እና የሙስና ተግባራት የልማቱ ዋነኛ ፈተና ሆነው መቆየታቸውንም ክብርት ሚኒስትሯ አብራርተዋል።

ወደ ገጽ 3 የዞረ

## ኢትዮጵያ በብሪክስ (BRICS) መድረክ አማካኝነት ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ትብብርን እያጠናከረች ነው



የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኢትዮጵያን በመወከል በሃይደራባድ፣ ህንድ በተካሄደው ሁለተኛው የBRICS ፀረ-ሙስና የሥራ ቡድን (ACWG) ስብሰባ ላይ በመሳተፍ ሙስናን ለመዋጋት በሚደረገው ዓለም አቀፍ ጥረት ውስጥ ያላትን ተሳትፎ አጠናክራለች። የBRICS አባል ሀገራት እና አጋሮች የውይይት መድረክ ሙስናን በመከላከል እና በመዋጋት ረገድ የተጠናከረ ትብብርን ለመወያየት፣ የህግ አስከባሪ ትብብርን በማጠናከር፣

ወደ ገጽ 4 የዞረ

# ተስፋን እንትከል በሚል መሪ ቃል የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች የችግኝ ተከላ አካሄዱ





የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከአዲስ አበባ ከተማ ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር በመተባበር "ተስፋን እንትከል' በሚል መሪ ቃል በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚከናወነውን በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ-ከተማ ወረዳ 3 (በተለምዶ አቃቂ ብረታ ብረት ፋብሪካ አካባቢ) የችግኝ ተከላ መርሃ-ግብር አካሄዱ::

በመርሃ-ግብሩ ላይ የተገኙት የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ክቡር ምክትል ኮሚሽነር ፍቃዱ ሰቦቃ፤ የመርሃ-ግብሩ መካሄድ የሰላም፣ የብልጽግና፣ የሕብረ-ብሔራዊ ተስፋንና የዛሬና የነገ ትውልዶችን መካከል የማስተሳሰር አቅም ያለው ሲሆን «ችግኝ በመትከል ችግርን መንቀል» የሚለውን ታላቅ አገራዊ ዓላማ ያነገበ መሆኑን ገልጸዋል::

በተመሳሳይ ኮሚሽነር እሸቴ አስፋው በበኩላቸው፤ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መሪነት የተጀመረው የአረንጓዴ አሻራ በዘንድሮው መርሃ-ግብር በአንድ ጀምበር 800 ሚሊዮን ችግኝ በመትከል የላቀ ድልና ተስፋ ማስመዝገቡን አብራርተዋል::

አያይዘውም በኮሚሽኑ ደረጃ 14 ሺህ ችግኞች መተከላቸውን በመጥቀስ፣ ለዚህ አገራዊና ተቋማዊ ሥራ ስኬት አስተዋጽኦ ላደረጉ አካላት በሙሉ ምስጋና አቅርበዋል::

በመርሃ-ግብሩ ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀማል ረዲ በበኩላቸው፤ ሀገራችን ለ8ኛ ጊዜ እያካሄደች በሚገኘው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ-ግብር የዘንድሮው የትኩረት አቅጣጫ ለምግብነት የሚያገለግሉ የችግኝ ዝርያዎችን በመምረጥ መትከል፣ ከጸደቁ በኋላም ተንከባክቦ ለውጤት ማብቃት ላይ ያተኮረ መሆኑን አስረድተዋል::

በተጨማሪም የአዲስ አበባ ከተማ ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮችና ሠራተኞች በዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ-ግብር ከፌዴራል ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ባለሙያዎች ጋር በጋራ በመሆን በቦታው በመገኘት ችግኞችን መትከላቸው ተገልጿል::

# UNODC ከፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር በመተባበር ለወጣቶች የአቅም ግንባታ ስልጠና ሰጠ






የተባበሩት መንግሥታት የዕፅ እና የወንጀል ቢሮ (UNODC) ከፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር በመተባበር በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን (ECA) አዳራሽ ለወጣቶች የአቅም ግንባታ ስልጠና ሰጥቷል::

ይህ አውደ-ጥናት በUNODC የGRACE (Global Resource for Anti-Corruption Education and Youth Empowerment) ኢኒሼቲቭ አማካይነት የተካሄደ ሲሆን ዋና ዓላማውም ሙስና በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ተቋማዊ መስኮች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ለወጣቶች ማስረፅን ጨምሮ በወጣቶች ዘንድ የሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ፣ የታማኝነት እና የምክንያታዊ አስተሳሰብ ክህሎትን ማጎልበት ነው:: በተጨማሪም ወጣቶች እምቅ አቅማቸውን፣ የፈጠራ እና የቴክኖሎጂ ብቃታቸውን ተጠቅመው ከፀረ-ሙስና ተቋማት ጋር በጥምረት እንዲሰሩ ለማስቻል ያለመ መሆኑ ተመላክቷል:: በዚህ የሁለት ቀናት የአቅም ግንባታ አውደ-ጥናት ላይ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተውጣጡ የተማሪዎች አምባሳደር፣ ከተለያዩ ተቋማት እና ከሲቪክ ማህበራት የተውጣጡ እድሜያቸው ከ18 እስከ 30 የሆኑ 25 ወጣቶች ተሳታፊ ሆነዋል::



# የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርሙ የመንግሥት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ግልጽነትና ተጠያቂነትን የሚያሻሽል መሆኑ ተገለጸ

የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርሙ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት የመንግሥት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓትንና የወጪ ውጤታማነትን ማሻሻሉን የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ክቡር አሕመድ ሽዴ ገለጹ::

ክቡር ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት ለመንግሥት ወጪ ቅልጥፍና፣ ለግልጽነትና ተጠያቂነት መጠናከር የጎላ ስትራቴጂካዊ ሚና አለው:: በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የመንግሥት የኤሌክትሮኒክ ግዥን በማስፋትና አሠራሮችን በማዘመን የተመዘገቡት አበረታች ውጤቶች በመንግሥት ወጪ ላይ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ያጠናከሩ ናቸው:: የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን በኤሌክትሮኒክ ግዥና በዲጂታላይዜሽን ያስመዘገባቸው ውጤቶች በመንግሥት ወጪዎች ላይ ያለውን ግልጽነትና ተጠያቂነት



የበለጠ የሚያጠናክሩ ናቸው ብለዋል:: ለሪፎርሙ ግብ መሳካት የመንግሥት ግዥ ሥርዓቱን ቀልጣፋ፣ ግልጽና ተጠያቂነት የሰፈነበት ማድረግ ያስፈልጋል:: የመንግሥት ሀብት የሕዝብ አደራ በመሆኑ፣ ይህንን አደራ በታማኝነት መጠበቅ የሁሉም የመንግሥት ተቋማት የመጀመሪያ ግዴታ ነው:: ሚኒስትሩ ይህንን ያሉት የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን የ2018 በጀት ዓመት የመንግሥት ግዥና ንብረት አፈጻጸምና የ2019 ዕቅድን በተመለከተ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፕሬዝዳንቶችና የሀብት አስተዳደር ኃላፊዎች ጋር ውይይት ባደረጉበት ወቅት ነው::

## 4ኛው አገራዊ...

ከገጽ 1 የዞረ

አጠቃቀም እና የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ዋና ዋናዎቹ ለሙስና የተጋለጡ ክፍሎች ናቸው:: በተለይም በመንግሥት ግዥ ሂደት ውስጥ 70 በመቶ ያህሉ ግ "ከአንድ አቅራቢ ብቻ የመግዛት" ልምድ የሚታይበት በመሆኑ ለሙስና ትልቅ በር መክፈቱ ተመልክቷል:: በአቋራጭ የመበልጸግ ፍላጎት፣ የሥነምግባር ዝቅጠት፣ የተንዛዛ አሰራር እና የሕግ ተገዥነት ማነስ ለችግሩ ዋና ምክንያቶች ሲሆኑ፤ ጉዳይን ማዘገየት፣ ጉቦና ሥልጣንን አላግባብ መጠቀም ደግሞ ዋና ዋና መገለጫዎች እንደሆኑ በጥናቱ ተመላክቷል::

በጥናቱ ከተሳተፉት መካከል 62 በመቶ የሚሆኑት መንግሥት ሙስናን ለመዋጋት ቁርጠኝነት እንዳለው የገለጹ ቢሆንም፤ ነገር ግን ለሙሰኞች የሚሰጠው ቅጣት አስተማሪ አይደለም የሚል እምነት አላቸው:: በተጨማሪም የተመዘበረ ሀብትን በማስመለስ እና ለጠቋሚዎች የሚደረግ የሕግ ከለላ ላይ አሁንም ሰፊ ክፍተቶች መኖራቸው ተጠቅሷል:: በሌላ በኩል የቀረበው በብሄራዊ የሙስና መጠቆሚያ ስርዓት (NCRS) ሪፖርት እንደሚያመላክተው፣ ለኮሚሽኑ ከቀረቡ 630 የፌዴራል የሙስና ጥቆማዎች ውስጥ በፖሊስ፣ በፍትሕ ሚኒስቴር እና በፍርድ ቤቶች በኩል የምርመራና የክስ ሂደቶች ቢከናወኑም፤ የምርመራ መዝገቦች ጥራት ውስንነት፣ የፎረንሲክ ምርመራ ማነስ እና የተበጣጠሰ አሰራር እንቅፋት እንደሆነ በጥናቱ ተመላክቷል::

በተመሳሳይ በ38 ዩኒቨርሲቲዎች ላይ በተደረገው ዳሰሳዊ ጥናት፣ ዩኒቨርሲቲዎች ከፍተኛ የመንግሥት ሀብት የሚመደብላቸው በመሆናቸው ጥብቅ ቁጥጥር እንደሚፈልጉና የሰው ኃይል ምደባ ጥራት ሊረጋገጥ እንደሚገባ የኮሚሽኑ አመራሮች አሳስበዋል::

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ በሰጡት ማጠቃለያ፣ ጥናቱ የዜጎችን እውነተኛ ስጋት ያሳየ በመሆኑ ለፖሊሲ ግብዓትነት እንደሚያገለግል ገልጸዋል:: አያይዘውም፦ ምክረ ሀሳቦቹ ትኩረት ማድረግ ያለባቸው አገልግሎቶችን ሙሉ በሙሉ በዲጂታል ቴክኖሎጂ ማዘመን፣የሕግ ማስከበር አቅምን ማጠናከርና የሙስና ወንጀል ልዩ ችሎቶችን ማጠናከር፣ የሹመትና የቅጥር ሂደቶች በሥነምግባር ምዘና እንዲያልፉ ማድረግ፣ እና የተመዘበረ ሀብትን ለማስመለስ የፍትሕ እና የፖሊስ ተቋማት በዲጂታል ሥርዓት ተቀናጅተው መስራት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል::

# ኮሚሽኑ በቀጣይ አወንንታዊ ሙስናን የመከላከል ስትራቴጂ በመከተል ይሰራል - ኮሚሽነር ማሞ ቴጋ




የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የ2018 በጀት እቅድ አፈፃፀም ግምገማና የ2019 በጀት ዓመት መሪ እቅድን ትኩረት ያደረገ የምክክር መድረክ በወልቂጤ ከተማ አካሂዷል።

በመድረኩ ላይ የማዕከላዊ ኢትዮድያ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ማሞ ቴጋ ባደረጉት ንግግር፤ ኮሚሽኑ በዓመቱ አበረታች ተግባራት ማከናወኑን ገልፀዋል። በዚህም በጠቅላላው 336 ሚሊዮን 231 ሺ 934 ብር ከብክነትና ምዝበራ ማዳን መቻሉን ኮሚሽነር ማሞ ጠቁመዋል። ከዚህ ባለፈ በዓይነት በድምሩ ሁለት አምቡላንስን ጨምሮ ከ2 ሺ 613 ሄክታር በላይ የገጠር መሬትና 256 ሺ 932 ካሬ ሜትር የከተማ መሬት በኮሚሽኑና በታችኛው መዋቅር ከብክነት መታደግ መቻሉን አውስተዋል።

በበጀት ዓመቱ 13 ሺ 5 መቶ አመራርና ሰራተኞች ሀብትና ንብረታቸውን እንዲያስመዘግቡ መደረጉን ኮሚሽነር ማሞ አስታውቀዋል። በቀጣይም አወንታዊ ሙስናን የመከላከል ስትራቴጂ በመከተል ይሰራል ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ለዘርፉ ውጤታማነት ሁሉም የበኩሉን እንዲወጣ አሳስበዋል። ከመድረኩ ተሳታፊዎች መካከል አቶ ፍትህአወቅ ፋንታሁንና አቶ ታረቀኝ ዋኖሬ በሰጡት አስተያየት፤ መድረኩ ስራዎቻቸውን በጥልቀት ለመገምገም እንዳስቻላቸው ጠቁመዋል። አስተያየት ሰጪዎቹ አክለውም ሙስናና ብልሹ አሰራር ሀገራዊ ልማትን የሚያደናቅፍ በመሆኑ ችግሩን ለመቀነስ ሁሉም የድርሻውን መወጣት አለበት ብለዋል።

በመድረኩ ላይ በኮሚሽኑ በቀረበው የ2018 በጀት አመት የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ዙሪያ ውይይት የተደረገ ሲሆን ለተነሱ ጥያቄዎችም በባለድርሻ አካላት ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቷል። በምክክር መድረኩ ላይ የኮሚሽኑ አመራሮች፣ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፤ የክልል፣ የዞንና ልዩ ወረዳ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ዳይሬክተሮችና ቡድን መሪዎች ተሳትፈዋል።

## በሙስናና ሕገ-ወጥ አሠራር የተሳተፉ አካላት...

ከገጽ 1 የዞረ

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፣ የሕገ-ወጥነት ችግር በአንድ ወገን ብቻ የሚፈጸም ሳይሆን በርካታ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚያጠቃልል መሆኑን ገልጸው፣ ከውስጥም ከውጪም ያሉ በርካታ ኃይሎች በተደራጀ መንገድ ሲንቀሳቀሱ ነበር። በንግዱ ማኅበረሰብ፣ በልማት ድርጅቶች፣ በመንግሥት መዋቅር፣ በግለሰቦች እና በተገልጋዮች ጭምር በተደራጀ መንገድ በስፋት የሚታይ ነው።

እነዚህ አካላት ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያውን ከቁጥጥር ውጭ ለማድረግ በፋይናንስ እና በንግድ ሥርዐቱ ውስጥ ሰርገው በመግባት ከፍተኛ የኢኮኖሚ አሻጥር ሲፈጽሙ ቆይተዋል" ያሉት ወይዘሮ እናትዓለም፤ ድርጊቱ ሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬ እንድታጣ፣ የዋጋ ንረትና ኮንትሮባንድ እንዲባባስ እንዲሁም በፍጆታ እቃዎች ላይ ሰው ሠራሽ እጥረት እንዲፈጠር ማድረጉን አስታውቀዋል። ይህንን የተደራጀ አሻጥር ለመግታት መንግሥት እና የሚመለከታቸው የሕግ አካላት ባከናወኑት ሰፊ ኦፐሬሽን አሻጥሩን ማክሸፍ መቻሉ ተገልጿል።

በሌላ በኩል በመንግሥት አገልግሎት ሰጪ እና አስተዳደር አካላት እንዲሁም የሕዝብ ተቋማት ውስጥ የተሰገሰጉ ሌቦችን በማጽዳት ረገድ መንግሥት ቁርጠኛ እርምጃ እየወሰደ እንደሚገኝ ያስታወቁት ወ/ሮ እናትዓለም በሕዝብ ሀብት ላይ ከፍተኛ ምዝበራ የፈጸሙ እና ተቋማዊ አሻጥር በሠሩ አመራሮች እና ሌሎች የጥቅም ትስስሮችና ድርጅቶች ላይ የማያዳግም እርምጃ መወሰዱንም አስታውቀዋል። በተለይም በሚከተሉት ቁልፍ ዘርፎች ላይ በተፈጸሙ ወንጀሎች ሰፊ ማጣራት ተደርጎ ተጠያቂነት ሰፍኗል ሲሉ ገልጸዋል።

በመንግሥት አገልግሎት ሰጪ እና አስተዳደር አካላት፣ እንዲሁም ልዩ ልዩ የልማት ዘርፎች ውስጥ የተፈጸሙ ዋና ዋና የሙስና እና አሻጥር ወንጀሎችን ለማረም በተወሰዱት ሰፊ ኦፐሬሽኖች እና ሕግ የማስከበር እርምጃዎች ተጨባጭ ውጤቶች ተመዝግበዋል።

ከማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ጋር በተያያዘ ማሻሻያውን ለማደናቀፍ በማሰብ መሠረታዊ የፍጆታ ምርቶችን በማከማቸት እጥረት እንዲፈጠርና ዋጋ እንዲንር ሲያደርጉ የነበሩ 13 አቅራቢ ድርጅቶች ባለቤቶች ላይ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል፤ ሕገ-ወጥ ተግባር ሲፈጽሙ በነበሩ ከ7 ሺህ በላይ የንግድ ድርጅቶችና መጋዘኖች ላይ የማሸግ እርምጃ ተወስዷል።

በፋይናንስ ተቋማት እና የገንዘብ ዝውውር፡- በሕገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር፣ በሐዋላ እና በጥቁር ገበያ ተሳታፊ የሆኑ 169 ኢትዮጵያውያንና የውጭ ሀገር ዜጎች በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ተደርጓል። በተደራጀ መንገድ ከንግድ ባንክ ደንበኞች አካውንት ላይ በማጭበርበር ገንዘብ የወሰዱ 36 ግለሰቦች በቁጥጥር ስር ውለው የባንክ ሒሳባቸው እንዲታገድ ተደርጓል።

ለሕገ-ወጥ ዝውውር ሽፋን ይሰጡ የነበሩ 7 የክሪፕቶ ካረንሲ መተግበሪያዎች በሀገር ውስጥ እንዳይሠሩ ሙሉ በሙሉ ታግደዋል፤ ምርት ልከው የውጭ ምንዛሬ ተመላሽ ያላደረጉ 29 ላኪ የንግድ ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይም የህግ ተጠያቂነት ሰፍኗል።

በቤቲንግ እና ፊንቴክ ቢዝነሶች፡- የደንበኞችን መረጃ በመደበቅ መንግሥትን ግብር ያጭበረበሩ፣ ገቢያቸውን የሰወሩ እና ሕገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር በፈጸሙ 38 የቤቲንግ ድርጅቶች ላይ እርምጃ ተወስዶ ባለቤቶቻቸው በቁጥጥር ስር ውለዋል፤ የእነዚህ ሕገ-ወጥ ተቋማት የባንክ ሒሳብ ታግዷል።

በማዕድን ዘርፍ ሕገ-ወጥ ዝውውር፡- የወርቅ ምርትን ከገበያ ውጭ በኮንትሮባንድ በማስወጣት ወንጀል የተሳተፉ የመንግሥት ኃላፊዎችን፣ የፀጥታ መዋቅር አመራሮችን፣ አምራቾችን እና የውጭ ዜጎችን ጨምሮ 183 ግለሰቦች በሕግ ተጠያቂ ተደርገዋል። በወንጀሉ የተሳተፉ የውጭ ሀገር ዜጎች ከሀገር እንዲወጡ ተደርገዋል፤ ሕገ-ወጥ ወርቅ፣ የወርቅ ሚዛንና ማቅለጫ፣ የተለያዩ የውጭ ሀገራት ገንዘቦች፣ እንዲሁም የጦር መሳሪያዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል።

ከነዳጅ አቅርቦት እና ሎጂስቲክስ አንጻር፡- በሕገ-ወጥ መንገድ የሽፋን ደብዳቤዎችን በማዘጋጀት፣ ነዳጅ በመደበቅ እና አየር በአየር በመሸጥ ወንጀል የተሳተፉ 38 የመንግሥት አመራሮች በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ተደርጓል። በተጨማሪም በሀገር አቀፍ ደረጃ በሕገ-ወጥ የነዳጅ ንግድ ላይ የተሰማሩ ከ650 በላይ ግለሰቦች፣ ማደያዎች እና አቅራቢ ኩባንያዎች ላይ የህግ እርምጃ ተወስዷል።

በአፈር ማዳበሪያ ግዢ አሻጥር፡- በተቋሙ የጥቅም ትስስር በመፍጠር ጥራት የጎደለውና ጊዜው ያለፈበት የአፈር ማዳበሪያ ግዢ እንዲፈጸም በማድረግ ሆን ብለው ችግር በፈጠሩ የግብርና ሚኒስቴር አመራሮች ላይ የወንጀል ተጠያቂነት እርምጃ ተወስዷል።

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (EEP)፡- ተገቢው መመሪያ በሌለበት ሁኔታ ከ36 የዳታ ማይኒንግ ድርጅቶች ጋር ሕገ-ወጥ የኃይል ሽያጭ ውል የፈጸሙ 4 ከፍተኛ አመራሮች ላይ እርምጃ ተወስዷል። የኤሌክትሪክ ኃይል ስርቆት የፈጸሙ ድርጅቶች እና ግለሰቦችም እንዲሁ በሕግ እንዲጠየቁ ተደርጓል።

በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የሰዎች ዝውውር የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ሲስተምን በማዛባት እና ጉቦ በመቀበል ወንጀል የተሳተፉ 8 ከፍተኛ አመራሮችና ሠራተኞች በሕግ ቁጥጥር ስር ውለዋል። እንዲሁም በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ላይ የተሰማሩ 44 ደላሎች እና አዘዋዋሪዎች በሕግ ቁጥጥር ስር ሲውሉ፣ ሕገ-ወጥ ፈቃድ የነበራቸው ተቋማት ሙሉ በሙሉ ታሽገዋል።

በገቢዎችና ጉምሩክ ዘርፍ፡- የግብር ውሳኔዎችን በመቀነስ፣ ሐሰተኛ ደረሰኞች በማወራረድ፣ እና በሲስተም መረጃ በማጥፋት የመንግሥት ገቢን ባሳጡ አካላት ላይ ኦፐሬሽን ተካሂዷል።

በራሳቸው፣ በዘመድ እና በሹፌሮቻቸው አካውንት በመጠቀም የጥቅም ትስስር የፈጠሩ 109 ተጠርጣሪዎች ተለይተው ከእነዚህ መካከል 91 ግለሰቦች በሕግ ቁጥጥር ስር ውለዋል።

መንግሥት የልማት እንቅፋት የሆኑትን ሙስና እና ሌብነት እንደማንኛውም ፈተና በጽናት እየተጋፈጣቸው መሆኑን ሚኒስትሯ አረጋግጠዋል።

መንግሥት ሌብነትን ለማጥፋት ዘመናዊ አሠራሮችን በመዘርጋት እና በዲሲፕሊን የታነጸ አመራር ለመገንባት ቁርጠኛ ነው" ያሉት ወይዘሮ እናትዓለም፤ ሕዝቡ በስፋት የሚያነሣቸውን "ሌብነትን አስቁሙልን" ጥያቄዎች ለመመለስ የተጀመረዉ ጠንካራ እርምጃ ውጤታማ እንዲሆኑ ማኅበረሰቡ ሙስናን በማጋለጥ፣ ሕጋዊ መብቱን በመደለያ ባለመጠየቅ እና ከሕገወጦች ጋር ባለመተባበር ከመንግሥት ጎን በመቆም ሀገርን ከሕገወጥነትና ሙስና የመከላከል ታሪካዊ ኃላፊነቱን እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል።

## ምክር ቤቱ የክልሉን የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የ2019 በጀት ዓመት ጠቋሚ ዕቅድ አፀደቀ





የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት የክልሉን የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የ2018 በጀት ዓመት አፈፃፀምና የ2019 በጀት ዓመት ጠቋሚ ዕቅድ አፅድቋል:: የክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና የምክር ቤት አባል የሆኑት የተከበሩ አቶ ጥላሁን ከበደ ኮሚሽኑ ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚደርሱትን ጥቆማዎች መነሻ በማድረግ የሕዝብና የመንግስት ሀብት ከብክነት ለመከላከል ያከናወናቸው ተግባራት አበረታች ናቸዉ ብለዋል::

ተቋሙ ገለልተኛ ሆኖ ኃላፊነቱን እየተወጣ ለመሆኑ የክልሉ መንግስት እዉቅና ይሰጣል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ አሳስበዋል:: በክልሉ ለተለያዩ የልማት ስራዎች የሚመደበው ኃብት በአግባቡ ስራ ላይ እንዲዉል የፀረ ሙስና ትግሉ ተጠናክሮ እንዲቀጥልም ርዕሰ መስተዳድሩ አደራ ብለዋል:: ከዞኖች የሚመጡ ጥቆማዎችን በመቀበልና በመተንተን ተቋሙን የማጠናከርና በዲጂታል የማስደገፍ ስራ በመስራት ዉስን የሆነዉን የመንግስት ኃብት ማዳን እንደሚገባም ርዕሰ መስተዳድሩ በሰጡት አስተያየት አሳስበዋል::



## ሙያዊ ሥነምግባርንና ግልጽነትን በመገንባት የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል እየተሰራ ነው ተባለ



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በትምህርት ተቋማት የተጣለባቸውን ኃላፊነት በግልጽነት እና በሙያዊ ሥነ-ምግባር መወጣታቸውን የሚያረጋግጥ የ2018 የትምህርት ዘመን የማጠቃለያ ምዘና አካሄዷል::

ይህ ተቋማዊ አሰራርንና የሙያ ሥነ-ምግባርን መሰረት ያደረገ ምዘና ከቢሮው የሥራ ክፍሎች ጀምሮ በክፍለ ከተማና ወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤቶች፣ በአዳሪ ትምህርት ቤቶች፣ በሁሉም የመንግስት አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም በሱፐርቪዥን ክላስተር ማዕከላት ያካተተ ነው:: በየካ፣ ቦሌ እና አራዳ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤቶች እንዲሁም በእቴጌ መነን የልጃገረዶች አዳሪ ትምህርት ቤት ተገኝተው የምዘናውን ሂደት የተመለከቱት የቢሮ ኃላፊ አማካሪና የዘርፉ አስተባባሪ ወይዘሮ አበበች ነጋሽ እንደገለጹት፤ ወቅታዊና ገለልተኛ ምዘናዎችን ማካሄድ በአገልግሎት አሰጣጥ የረካ የትምህርት ማህበረሰብ ለመፍጠር፣ የተማሪዎችን የትምህርት ውጤትና የሥነ-ምግባር ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ ለማሻሻል ይረዳል::

አማካሪዋ አያይዘውም፣ ተቋማዊ አሰራርንና ግልጽነትን ለማስፈን ቢሮው በበጀት ዓመቱ ተደጋጋሚ የድጋፍና ክትትል ስራዎችን ሲያከናውን መቆየቱን ጠቁመው፤ የአንደኛ መንፈቅ ዓመት አፈጻጸምን መሰረት በማድረግ የተሻለ ሥነ-ምግባርና አፈጻጸም ላስመዘገቡ ተቋማት ዕውቅና መሰጠቱን አስታውሰዋል:: የምዘናው ሂደት ፍፁም ገለልተኛ እና ፍትሃዊ እንዲሆንም አስቀድሞ በመዛኝነት ለሚሳተፉ ባለሙያዎች በቂ ኦሬንቴሽን መኖሩን ገልጸዋል:: የሪፎርም ስራዎች ዳይሬክተር አቶ ፈንታሁን እያዩ በበኩላቸው፣ ምዘናው በተቋማት የቁልፍ ተግባራት አመላካች (KPIs) እና በሪፎርም አፈጻጸም ላይ የተመሰረተ በመሆኑ፣ የተቋማትን ተጠያቂነትና የአገልግሎት ጥራት የሚያረጋግጥ ነው ብለዋል::



## ኢትዮጵያ በብሪክስ (BRICS) መድረክ...

ከገጽ 1 የዞረ







ከሙስና ጋር የተያያዙ ወንጀኞችን በመከታተል እና የርክክብ ሂደቶችን ለማመቻቸት በሚደረጉ ጥረቶች ላይ በማተኮር ውይይት ተካሂዷል::

በሥራ ቡድኑ የውይይት መድረክ ወቅት ኢትዮጵያ ሙስናን በመዋጋት እና የሥነምግባር ግንባታን በማስተዋወቅ ረገድ ያላትን ተሞክሮ እና ቀጣይ እርምጃዎችን አጋርታለች:: ይህም ሀገሪቱ በዓለም አቀፍ አጋርነት አማካኝነት በሙስና ላይ የጋራ እርምጃ ለመውሰድ ያላትን ቁርጠኝነት አጉልቶ ያሳያል:: ኢትዮጵያን ወክለው በስብሰባው ላይ የተሳተፉት የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ እሸቱ አስፋው ኢትዮጵያ ሙስናን ለመከላከል እና ለመታገል የምታደርገውን ጥረት እና ያሏትን ተሞክሮዎችና ለፀረ-ሙስና ትግሉ የመንግስትን ቁርጠኝነት በመድረኩ ያቀረቡ ሲሆን፤ በብሪክስ ማዕቀፍ ውስጥ አብሮ ለመስራት ያላትን ቁርጠኝነትም አረጋግጠዋል::

የመድረኩ ተሳታፊዎቹም የBRICS መደበኛ ያልሆነ ትብብር ማዕከል ማቋቋም እና ከሙስና ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን ለመወጣት ኃላፊነት ባላቸው ተቋማት መካከል ቅንጅትን ለማሻሻል የህግ አስከባሪ ባለሙያዎች ኔትወርክ ማዘጋጀትን ጨምሮ የሥራ ተነሳሽነቶች ላይ ተወያይተዋል::

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ጋዜጣ

ስልክ 011552-77-79
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**
**EARS**

## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ሞባይል 0935947533
ፖ.ሳ.ቁ 34799

ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ኢ-ሜይል CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

NCRS

# ርዕሰ -አንቀፅ


## የአረንጓዴ አሻራን ማሳረፍ የዜግነትና የአካባቢ ጥበቃ ስነ-ምግባራዊ ግዴታ ነው!

8ኛው ዙር ብሔራዊ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በመላው ሀገሪቱ በድምቀት እየተካሄደ ይገኛል:: የዘንድሮውን የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ”ተስፋን እንትከል!‘ በሚል መሪ ቃል ሰኔ 8 ቀን 2018 ዓ.ም በቢሾፍቱ ከተማ በይፋ ያስጀመሩት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከከፍተኛ የመንግስት ስራ ኃላፊዎች ጋር በመሆን ነበር::

በዘንድሮው ዙር በመላ ሀገሪቱ በቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ ስራው በከፍተኛ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል:: ከዚህም ውስጥ በአንድ ጀንበር (በአንድ ቀን) ለመትከል የታቀደው ግብ 800 ሚሊዮን በላይ (800 Million) ችግኝ ተከላ ተከናውኗል:: አሁን ላይ ክረምቱን ተከትሎ በመላው ሀገሪቱ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ የመንግስትና የግል ተቋማት፣ የሀገር መከላከያ ሰራዊት እና ወጣቶች በየቀኑ በነቃ ሁኔታ ችግኝ የመትከል ስራውን እያካሄዱት ይገኛሉ:: መርሃ ግብሩ ከተጀመረበት ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ከ50 ቢሊዮን በላይ ችግኞች የተተከሉ ሲሆን፣ የዘንድሮውን 8 ቢሊዮን በመትከል ሀገራዊውን የ65 ቢሊዮን ችግኞች የረጅም ጊዜ ግብ ለማሳካት ሰፊ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል:: ከቀደሙት ዓመታት በተለየ መልኩ በዘንድሮው ተከላ ለምግብነት የሚውሉ የፍራፍሬ ችግኞች (እንደ አቮካዶ፣ ማንጎ፣ ፓፓያ እና ዘይቱን)፣ ለእንስሳት መኖ የሚያገለግሉ እና ለስነ-ምህዳር መጠበቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው ዕፅዋት በስፋት እየተተከሉ ይገኛሉ::

ከዚህም በተጨማሪ ችግኞችን ከመትከል ባሻገር የጸደቁትን የመንከባከብ፣ የውሃ አቅርቦት የማመቻቸት እና ጥበቃ የማድረግ ስራዎች አብረው እየተከናወኑ ነው:: የደን ሽፋንን ከማሳደግ ባሻገር የዘንድሮው ንቅናቄ የመሬት መሸርሸርን ለመከላከል እና ለገበያ የሚሆኑ ምርቶችን በማምረት የዜጎችን ገቢ ለማሻሻል ያለመ ነው:: የተፈጥሮ አካባቢን ከመጠበቅ ባሻገር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እና ዘላቂ ልማትን ለማምጣት ያለመው የ8ኛው ዙር ብሔራዊ መርሃ ግብር ስኬታማ እንዲሆን የመሬት አጠቃቀምን ህጋዊ ማድረግ፣ ለተከላ የተከለሉ ይዞታዎችን ከህገ-ወጥ ወረራ መጠበቅ እና የሚገኙ የፍራፍሬና የደን ውጤቶችን ለህብረተሰቡ በፍትሃዊነት ማከፋፈል የተቋማት የፍትሃዊነትና የሥነ-ምግባር ግዴታ ነው:: እያንዳንዱ ዜጋ የተፈጥሮ ሀብትን የመንከባከብ፣ የተተከሉ ችግኞችን የመጠበቅ እና ለቀጣይ ትውልድ ምቹ አካባቢን የመተው የዜግነትና የአካባቢ ጥበቃ ሥነ-ምግባራዊ ግዴታ አለበት:: በአጠቃላይ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ስኬታማ የሚሆነውና የታለመለት አላማ ላይ የሚደርሰው በሥነ-ምግባር የታነጸ ህብረተሰብ እና ከሙስና የጸዳ ግልጽ አሰራር ሲሰፍን ብቻ ነው:: የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያዎች እንደሚገልጹት፣ ”ተስፋን እንትከል!‘ የሚለው መሪ ቃል ለቀጣዩ ትውልድ ምቹ፣ ለም እና አረንጓዴ ሀገርን ለማስረከብ የሚደረግ ሀገራዊ ጥሪት ማሳያ ነው:: መርሃ ግብሩ በቀጣይም በሁሉም ክልሎች፣ ከተማ አስተዳድሮች እና በመላው የሀገሪቱ ክፍል ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ታውቋል:: በመሆኑም አረንጓዴ አሻራን በማኖር ስነምግባራዊ ግዴታችንን ልንወጣ ይገባል የሚል መልዕክት ኮሚሽኑ ያስተላልፋል::

**በሥነምግባር እና ሙስናን በመከላከል የቢሊዮን ችግኝ ተከላን በንቃት በመሳተፍ እናሳካ!**



# ቆይታ

## የሀገር ሀብትና የዜጎች መብት ጥበቃ በቴክኖሎጂ የተደገፈው የፀረ-ሙስና ትግል

ሙስና እና ብልሹ አሰራር የሀገርን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚያደናቅፉ፣ የተቋማትን ተስፋፊነት የሚያዳክሙና የዜጎችን እኩል የመልማት መብት የሚጋፉ አደገኛ ስጋቶች ናቸው:: እነዚህን የህዝብና የሀገር ጠንቆች ለመከላከል የሚደረገው ትግል ደግሞ የተወሰኑ ተቋማት ወሰን ብቻ ሳይሆን የጠቅላላው ማህበረሰብ ንቁ ተሳትፎን የሚጠይቅ የጋራ ኃላፊነት ነው::

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ይህንን ሀገራዊ ጥሪ መነሻ በማድረግ፣ የዜጎችን ተሳትፎ ለማሳደግ እና የግልጽነትና የተጠያቂነት አሰራርን ለማስፈን ዘመናዊ የዲጂታል አሰራሮችን በስፋት በመተግበር ላይ ይገኛል:: በተለይም በቅርቡ ስራ ላይ የዋለው ብሄራዊ የሙስና ወንጀል ጥቆማ ስርዓት (NCRS) ዜጎች ያለስጋትና ያለመረጃ ብክነት ጥቆማዎችን የሚያቀርቡበትን ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል::

በዚህ የጋዜጣችን ዕትም የዲጂታል ሙስና መረጃ አስተዳደር መሪ ስራ አስፈጻሚ አቶ መስፍን በላይነህ ጋር ያደረግነውን ሰፊ ቃለ-መጠይቅ አቀናጅተን አቅርበናል:: በቃለ-መጠይቁም የNCRS መተግበሪያ አጠቃቀም፣ የ25ቱ የሙስና ወንጀሎች ዝርዝር፣ ለጠቋሚዎችና ምስክሮች የሚደረገው የህግ ከለላ፣ እንዲሁም ከተመለሰው ሀብት እስከ 25 ፐርሰንት የሚደርሰው የማበረታቻ ክፍያ አፈጻጸም በስፋት ተዳሷል:: መልካም ንባብ!

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ:-** የኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ትግል ታሪካዊ አመጣጥ እና ህጋዊ ማዕቀፉ ምን ይመስላል?

**አቶ መስፍን በላይነህ:-** በኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ትግሉ በ1993 ዓ.ም. በተቋማዊ መልኩ ከተመሠረተ ጀምሮ በተከታታይ እየተከናወነ ይገኛል:: ይህም ሙስናን ለመከላከል፣ ለመመርመርና ለህግ ተጠያቂ ለማድረግ ልዩ ተቋማዊ አደረጃጀት የተፈጠረበትን ወሳኝ ምዕራፍ ያመለክታል:: ከዚያ በኋላ ሀገራችን ከዓለም አቀፍና ከአህጉራዊ የፀረ-ሙስና ሥርዓቶች ጋር ተጣጥማ ለመስራት ጠንካራ የሕግ መሠረት ፈጥራለች::

በዚህ መሠረት ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት የፀረ-ሙስና ስምምነትን በአዋጅ ቁጥር 445/1999 በማፅደቅ የሀገሪቱ ሕግ አካል አድርጋለች:: ይህ ስምምነት በሙስና መከላከል፣ በወንጀል ምርመራ፣ በወንጀለኞች ላይ የሕግ እርምጃ መውሰድ፣ በአገራት መካከል የሕግ ትብብር ማጠናከር እና ከወንጀል የተገኘ ንብረትን መልሶ ማስመለስ ረገድ አለም አቀፍ መስፈርቶችን ያስቀምጣል::

በተጨማሪም ኢትዮጵያ የአፍሪካ ህብረት የፀረ-ሙስና መከላከያና መዋጊያ ኮንቬንሽንን በመቀበል የሀገሪቱ ሕግ አካል አድርጋለች:: ይህም በአፍሪካ አገራት መካከል በፀረ-ሙስና ትግል የሚደረገውን ትብብር፣ የመረጃ ልውውጥ እና የጋራ የህግ ማስከበር ሥራዎችን ለማጠናከር ያግዛል:: ስለዚህ የኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ትግል በሀገራዊ ሕጎች ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍና በአህጉራዊ ሕጋዊ ማዕቀፎችም የተደገፈ ነው::

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ:-** ለመሆኑ በህጋችን መሠረት ሙስና ማለት ምን ማለት ነው? የስንት አይነት የሙስና ወንጀሎችስ ዝርዝር አለ?



**አቶ መስፍን በላይነህ:-** ሙስና ማለት በአብዛኛው አንድ የሥራ ኃላፊነት የተሰጠው ሰው የተሰጠውን ኃላፊነት ወይም ሥልጣን ከሕግና ከሥነ-ምግባር ውጭ በሆነ መንገድ በመጠቀም ለራሱ ወይም ለሌሎች ወገኖች ያልተገባ ጥቅም የሚያስገኝበት፣ ወይም በመንግሥት ሀብትና ንብረት ላይ ጉዳት የሚያደርስበት ሁኔታ ሲፈጠር ነው:: ይህ ያልተገባ ጥቅም በገንዘብ፣ በንብረት፣ በስጦታ፣ በአገልግሎት ወይም በሌላ ማንኛውም የግል ጥቅም መልክ ሊገለጽ ይችላል::

በሀገራችን የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2007 በግልጽ 25 የሙስና ወንጀሎችን ይደነግጋል:: ይህ የህግ ማዕቀፍ በመንግሥት ተቋማትና በሕዝብ ሀብት ላይ የሚፈጸሙ የተለያዩ የሙስና ተግባራትን በዝርዝር ይገልጻል:: ከእነዚህም መካከል ሥልጣንን ካላግባብ መጠቀም፣ ጉቦ መቀበል ወይም መስጠት፣ የማይገባ ጥቅም መቀበል፣ ሥራን በማያመች አኳኋን መምራት፣ ሀሰተኛ ሰነድ መገልገል እና ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ማፍራት ተጠቃሽ ወንጀሎች ናቸው:: እነዚህ ወንጀሎች የመንግሥት ሀብትን ከመጉዳት ባለፈ በሕዝብ የመንግሥት አመኔታ፣ በፍትሃዊ አገልግሎት አሰጣጥ እና በሀገር ልማት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራሉ::

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ:-** የፀረ-ሙስና ትግሉ በምን ያህል ዋና ዋና ስትራቴጂዎች ተከፍሎ ነው እየተከናወነ ያለው?

**አቶ መስፍን በላይነህ:-** የፀረ-ሙስና ትግሉ በሶስት ዋና ዋና ስትራቴጂዎች ተከፍሎ ይሰራል:: እነዚህ ስትራቴጂዎች እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ ሲሆን ዓላማቸውም ሙስናን ከመከላከል ጀምሮ እስከ ህግ ማስከበር ድረስ ያለውን ሂደት በተቀናጀ መንገድ ማስፈጸም ነው::

1. የሥነ-ምግባር ግንባታ: ዜጎች፣ ወጣቶች እና ሕፃናት ሙስናን በአመለካከትም ሆነ በተግባር የሚያፀየፉ እንዲሆኑ በተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች፣ በሥነ-ምግባር ትምህርቶች፣ በሚዲያ ዘመቻዎች እና በተቋማት የእሴት ግንባታ ሥራዎች አማካይነት ታማኝነት፣ ተጠያቂነት እና የሕዝብ ሀብትን የመጠበቅ ባህል እንዲዳብር ይሰራል::

2. የሙስና ቅድመ መከላከል: በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና በልማት ድርጅቶች ውስጥ የአሠራር ሥርዓት ጥናት በማካሄድ ለሙስና የሚያጋልጡ ድክመቶችን መለየት፣ የሀብትና የገቢ ምንጭ ምዝገባን ማስፈጸም፣ የሙስና ስጋቶችን መለየት እና ማስተካከያዎችን በማድረግ የሙስና መከሰት አጋጣሚን የመቀነስ ሥራ ይሰራል::

3. ህግ ማስከበር: ሙስና ወንጀል ተፈጽሞ ወይም ተፈጽሟል ተብሎ ሲጠረጠር አስፈላጊውን የህግ ማስከበር ሥራ ይከናወናል:: ይህም ጥቆማ ከመቀበል ጀምሮ የወንጀል ምርመራ፣ ክስ መመስረት፣ የፍርድ ሂደት፣ የውሳኔ አፈጻጸም እና በሙስና ወንጀል የተገኘ ንብረትን እስከማስመለስ ያለውን የህግ ሂደቶችን ያካትታል:: ዓላማውም ሙሰኞችን ለሕግ ማቅረብ፣ የሕዝብ ሀብትን ማስመለስ እና የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ ነው::

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ:-** ዜጎች በጥቆማ አሰጣጥ ወቅት የሚያጋጥማቸውን የስጋትና የመረጃ ብክነት ችግር ለመቅረፍ ኮሚሽኑ ምን አዲስ የቴክኖሎጂ አሰራር ዘርግቷል?

**አቶ መስፍን በላይነህ:-** ቀደም ሲል የሙስና ወንጀል ጥቆማዎች በአካል በመቅረብ፣ በወረቀት በመፃፍ ወይም በተለመዱ የመገናኛ መንገዶች ይቀርቡ ነበር:: ይህ አሰራር በአንዳንድ ጊዜ የመረጃ መዘግየት፣ የወረቀት መጥፋት፣ የመረጃ ብክነት እና የጠቋሚዎች ማንነት ሊገለጥ ይችላል የሚል ስጋት ይፈጥር ነበር:: በመሆኑም ዜጎች ያለፍርሃት፣ በሚያምኑበት እና

በምስጢራዊነት የተጠበቀ መንገድ ጥቆማ እንዲያቀርቡ የሚያስችል ዘመናዊ የዲጂታል ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ።

ይህንን ለመቅረፍ ኮሚሽኑ ከኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር "NCRS" (ብሔራዊ የሙስና ወንጀል ጥቆማ ሥርዓት) የተሰኘ ዘመናዊ የዲጂታል መተግበሪያ አዘጋጅቶ ከ2017 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ሥራ አስገብቷል። ይህ ሥርዓት የጥቆማ አሰጣጥን ዲጂታላዊ በማድረግ መረጃዎች በፍጥነት እንዲደርሱ፣ በደህንነት እንዲጠበቁ እና በሥርዓት እንዲተዳደሩ ያስችላል።

በዚህ ሲስተም ዜጎች ከየትኛውም ቦታ ሆነው፣ በማንኛውም ጊዜ በስማርት ስልካቸው ወይም በሌሎች የዲጂታል መገናኛ መሳሪያዎች በመጠቀም በፅሁፍ፣ በፎቶ ወይም በቪዲዮ የተደገፈ ጥቆማ መላክ ይችላሉ። ጥቆማው እንደደረሰም ለእያንዳንዱ ጠቋሚ ልዩ የቲኬት ቁጥር (Ticket Number) ይሰጠዋል። ይህ የቲኬት ቁጥር ጥቆማው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለመከታተልና ሂደቱን በግልጽ ሁኔታ ለማወቅ ያገለግላል። መረጃው ሙሉ በሙሉ በሲስተሙ ውስጥ ስለሚቀመጥ፣ የመረጃ ብክነት፣ የወረቀት መጥፋት ወይም የፋይል መዘግየት የመሳሰሉ ችግሮች በእጅጉ ይቀንሳሉ።

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- በNCRS የተላከ ጥቆማ ከተተነተነ በኋላ ቀጣይ ሂደቱ እንዴት ይፈጸማል? ከፖሊስና ሌሎች አካላት ጋር ያለው ትስስር እንዴት ነው?

አቶ መስፍን በላይነህ፡- ጥቆማው ወደ ሲስተሙ እንደደረሰ በመጀመሪያ በባለሙያዎች ይተነተናል። የቀረበው መረጃ በቂ መሆኑ፣ ከሙስና ወንጀል ጋር ያለው ግንኙነት እና የሚፈለጉ ተጨማሪ መረጃዎች ካሉ ይገመገማሉ። የመጀመሪያ ትንተናው ከተጠናቀቀ በኋላ ለጠቋሚው በሲስተሙ አማካኝነት የመጀመሪያ ምላሽ ይሰጣል።

በዚህም መሠረት መረጃው የሙስና ወንጀል መሆኑ ከታወቀ "ሙስና ነው"፣ አደጋ የሚያመለክት ነገር ካለ "ወደ ሙስና እየሄደ ነው"፣ ከሙስና ወንጀል ጋር የማይገናኝ ከሆነ ደግሞ "ሙስና አይደለም" የሚል የመጀመሪያ ምላሽ ለጠቋሚው በስልኩ ይደርሰዋል። ይህ ሂደት ጠቋሚው ጥቆማው ተቀብሎ በሂደት ላይ መሆኑን እንዲያውቅና በተቋሙ ላይ የበለጠ እምነት እንዲኖረው ይረዳል።

ሙስና መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ እንደቀድሞው ዘዴ ደብዳቤ ተጽፎ በመዝገብ ቤት በኩል ከመተላለፍ ይልቅ በቀጥታ በሲስተሙ አማካኝነት ለፌዴራል ፖሊስና ለሚመለከታቸው የፍትህ አካላት ይተላለፋል። ይህ የዲጂታል ትስስር የሰነድ ዝውውርን በማፋጠን የምርመራ ሥራው በአጭር ጊዜ እንዲጀመር ያስችላል። ከመስከረም 2017 ዓ.ም. ጀምሮም ለፌዴራል ፖሊስ የሚተላለፉ መረጃዎች ሙሉ በሙሉ በዲጂታል አሰራር እየተከናወኑ ይገኛሉ። በተጨማሪም ይህ ሲስተም በአንድ ማዕከል የሚሰጡ የመንግሥት አገልግሎቶች ውስጥም እየተካተተ በመሄድ ለዜጎች የተሻለ ተደራሽነትና ቅልጥፍና ለመፍጠር እየተሠራ ነው።

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- አንድ ዜጋ በNCRS መተግበሪያ ጥቆማ መስጠት ቢፈልግ ደረጃ በደረጃ እንዴት ነው መጠቀም የሚችለው?

አቶ መስፍን በላይነህ፡- የመተግበሪያው አጠቃቀም በጣም ቀላል ሲሆን ማንኛውም ዜጋ አነስተኛ የዲጂታል እውቀት ብቻ በመጠቀም ጥቆማውን ማቅረብ ይችላል። የጥቆማ አቀራረቡ ደረጃ በደረጃ እንዲህ ነው፦

1. በስማርት ስልክ Play Store ወይም App Store ውስጥ በመግባት NCRS ብለው ይፈልጋሉ፤ ከዚያም መተግበሪያውን Install በማድረግ በስልካቸው ላይ ይጭናሉ።

2. መተግበሪያውን ከከፈቱ በኋላ ሙሉ ስም፣ የስልክ ቁጥር እና በስልካቸው የሚላከውን የOTP ማረጋገጫ ኮድ በማስገባት ምዝገባቸውን ያጠናቅቃሉ።

3. ወደ ሲስተሙ ከገቡ በኋላ በሕግ የተደነገጉትን 25 የሙስና ወንጀሎች ዝርዝር ያያሉ፤ ከዚህም በጥቆማቸው የሚመለከተውን የወንጀል አይነት ይመርጣሉ።

4. ከዚያ በመቀጠል የጠቆሙበትን ግለሰብ ሙሉ ስም፣ የሥራ ኃላፊነት፣ የሚሰራበትን ተቋም እና ክስተቱ የተፈጸመበትን ሁኔታ በተቻለ መጠን በግልጽ ያስገባሉ።

5. በመጨረሻ የፅሁፍ፣ የፎቶ ወይም የቪዲዮ ማስረጃዎች ካሉ አያይዘው Submit ያደርጋሉ። ከዚያ በኋላ ሲስተሙ የሚሰጣቸውን ልዩ የቲኬት ቁጥር በመያዝ ጥቆማቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በቀጣይነት መከታተል ይችላሉ። ይህም ሂደቱን ግልጽ፣ ተገማች እና ለተጠቃሚዎች ቀላል የሚያደርግ ዘመናዊ የዲጂታል የጥቆማ አሰጣጥ ሥርዓት ነው።

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- የሙስና ወንጀል ጠቋሚዎችና ምስክሮች የሚያገኙት የህግ ከለላና የማበረታቻ ስርዓት በህጉ እንዴት ተደንግጓል?

አቶ መስፍን በላይነህ፡- የሙስና ወንጀልን ለመከላከልና ለማጋለጥ የዜጎች ተሳትፎ እጅግ ወሳኝ በመሆኑ፣ በትክክለኛ መረጃ ላይ ተመስርተው ጥቆማ የሚያቀርቡ ጠቋሚዎችና ለፍትህ ሂደት ምስክርነት የሚሰጡ ሰዎች በማንኛውም አይነት ጫና፣ ዛቻ፣ በቀል ወይም አድልዎ እንዳይደርስባቸው ህጉ ልዩ ጥበቃ አስቀምጧል። በመሆኑም ጠቋሚዎቻችንና ምስክሮቻችን በራሳቸው፣ በቤተሰባቸው ወይም በሥራ ገበታቸው ላይ ጫና እንዳይደርስባቸው በወንጀል ጠቋሚዎችና ምስክሮች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 699/2003 መሠረት ኮሚሽኑ ከፍትህ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር አስፈላጊውን ሙሉ የህግ ከለላ እንዲያገኙ ያደርጋል።

ይህ የህግ ጥበቃ ጠቋሚዎችና ምስክሮች በፍርሃት ሳይሸማቀቁ እውነተኛ መረጃ እንዲያቀርቡ፣ በፍትህ ሂደትም ያለምንም ጫና እንዲተባበሩ የሚያግዝ ነው። በህጉ መሠረት የጠቋሚዎችና የምስክሮች ማንነትና ግላዊ መረጃ በሚገባ ይጠበቃል፤ አስፈላጊ ሲሆንም ተጨማሪ የደህንነት ጥበቃ እርምጃዎች በሚመለከታቸው ተቋማት በኩል ይወሰዳሉ። ይህም የህግ ከለላ የዜጎችን እምነት በማጠናከር የሙስና ወንጀል ማጋለጥ እንዲበረታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

በተጨማሪም የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 668/2002 እና የሀብት ማስመለስ አዋጅ ቁጥር 1364/2017 በግልፅ እንደተደነገገው ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን ለሚያጋልጡ ዜጎች የማበረታቻ ሥርዓት ተዘርግቷል። በዚህ መሠረት በጥቆማቸው ምክንያት የተገኘና ወደ መንግስት የተመለሰ ሀብት ካለ፣ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ከተመለሰው ሀብት እስከ 25 በመቶ የሚደርስ የማበረታቻ ጉርሻ እንደሚሰጥ በህግ ተመላክቷል።

ይህ የማበረታቻ ሥርዓት ዜጎች የሀገርን ሀብት ለመጠበቅና የሙስና ወንጀሎችን በወቅቱ ለማጋለጥ ያላቸውን ተነሳሽነት ለማጠናከር የተዘረጋ ነው። ከዚህ በተጨማሪም የሚሰጠው ሽልማት ለግል ጥቅም ሳይሆን የህዝብና የመንግስት ሀብት እንዲጠበቅ የሚደረገውን የዜግነት አስተዋጽኦ ለማበረታታት የተዘረጋ ህጋዊ አሰራር ነው።

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- በመጨረሻም የሚያስተላልፉት ጥሪ ካለ?

አቶ መስፍን በላይነህ፡- ሙስና የሀገርን ኢኮኖሚ፣ የመንግስት ተቋማትን ተዓማኒነት፣ የህዝብን እምነትና የልማት እድሎችን የሚጎዳ ከባድ አደጋ ነው። ለዚህም ነው ሙስናን የሀገርንና የህዝብን ሀብት የሚበላ፣ የጥቂቶችን ጥቅም አስክብሮ የብዙሃኑንን የሚጎዳ "የሚጣፍጥ መርዝ" በማለት የምንገልፀው። በመሆኑም የሙስና ወንጀልን መከላከልና ማጋለጥ የአንድ ተቋም ብቻ ሳይሆን የሁሉም ዜጎች የጋራ ኃላፊነት ነው።

ስለዚህ ዜጎች ተስፋ ሳይቆርጡ፣ በእውነተኛ መረጃና በበቂ ማስረጃ ላይ ተመስርተው የሙስና ወንጀሎችን ማጋለጥ ይጠበቅባቸዋል። ትክክለኛ መረጃ በወቅቱ መቅረቡ የመንግስት ሀብት ከብክነት እንዲድን እና ተገቢው የህግ ማስከበር ሥራ እንዲከናወን ያስችላል።

ዜጎች ሳያመነቱ ህጋዊ መብታቸውን በመጠቀም የሙስና ወንጀሎችን ሲያጋልጡ፣ ተቋማችንም በህጉ መሠረት አስፈላጊውን የጥበቃና የህግ ከለላ እንዲያገኙ የሚያደርግ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

በመጨረሻም ሁሉም ዜጋ በየደረጃው የዜግነት ኃላፊነቱን በመወጣት፣ ሙስናን በማጋለጥ፣ የህዝብ ሀብትን በመጠበቅ እና ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነባት ኢትዮጵያ ለመገንባት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ጥሪ አቀርባለሁ።

## አመሰግናለሁ!

# ሳይቃጠል በቅጠል

## የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት የመኝታ ክፍሎች እድሳት ግዥ ጨረታ ላይ የተፈፀሙ ጥሰቶች

የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት የመኝታ ክፍሎች እድሳት ግዥ ጨረታ ላይ የተፈፀሙ ጥሰቶች

የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት በቢሾፍቱ የስልጠና ማዕከሉ በሚገኙ 72 የመኝታ ክፍሎች እድሳት ሂደት ላይ የግዥ አወጅና መመሪያን ባልተከተለ መልኩ የአሰራር ግድፈት መፈጸሙን የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናት አጋልጧል። በኮሚሽኑ ብሔራዊ የሙስና መረጃ ሪፖርት ሥርዓት (NCRS) በደረሰ ጥቆማ መሰረት በተደረገ ፈጣን ማጣራት በኢንስቲትዩቱ ከ45 ሚሊዮን ብር በላይ ዋጋ ያለውን የግንባታ እድሳት ባልተገባ መንገድ በውስን ግዥ ጨረታ ለመስጠት መሞከሩ ተረጋግጧል።

በግልጽ ጨረታ ተካሂዶ መጠናቀቅ የነበረበት የ45 ሚሊዮን ብር የልማት ፕሮጀክት፣ አሰራርን ባልተከተለ መንገድ ወደ “ውስን ጨረታ” እንዲቀየር መደረጉ እና ቀደም ሲል በውል ጥሰት ስሙ የተነሳ ድርጅት በድጋሚ አሸናፊ እንዲሆን መደረጉ በሪፖርቱ በጥብቅ ከተነሱት ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ይህ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናት ሪፖርት በኢንስቲትዩቱ የመኝታ ክፍሎች እድሳት ግዥ ላይ የተፈጸመ የሕግና የአሰራር ጥሰትን ያመላክታል። ተቋሙ በቂ ጊዜ እያለው “የጊዜ እጥረት” በሚል ሽፋንና የውስን ጨረታ ሕጋዊ ጣሪያ የሆነውን 18 ሚሊዮን ብር በመጣስ የ45.59 ሚሊዮን ብር ፕሮጀክት በውስን ጨረታ እንዲከናወን ተደርጓል። በተጨማሪም የቴክኒክ ምዘናውና የመሃንዲስ ግምቱ በአንድ ባለሙያ ብቻ የተሰራ ሲሆን ሕጋዊ ማስረጃ የሌላቸው ተቋራጮች በውድድሩ እንደተሳተፉ ማየት ተችሏል ::

በሌላ በኩል አሸናፊ የተባለው ሳበርኮን ኢንጂነሪንግ ቀደም ሲል በነበሩ ፕሮጀክቶች ውል የተቋረጠበት፣ ተቋሙን የ18 ሚሊዮን ብር ገቢ ማሳጣቱ በተቋሙ የተገለፀ እና ያለ በቂ ሰነድ ክፍያ የተፈጸመለት ሆኖ ሳለ በድጋሚ እንዲሳተፍ ተደርጓል። በመጨረሻም የተቋሙ የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ የግዥ አሠራር ጥሰት በመታዘቡ ጨረታውን ውድቅ ቢያደርገውም የአስተዳደሩ የበላይ አካላት የኮሚቴውን ውሳኔ ወደ ጎን በማለት ሥራውን በቀጥታ ለተቋራጩ መስጠታቸው በጥናት ተለይቷል።

### የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች

ኢንስቲትዩቱ ጨረታውን ወደ ውስን ጨረታ ከመውሰዱ በፊት በግልፅ ጨረታ አለማውጣቱ፣ ኢንስቲትዩቱ የምህንድስና ዋጋ ግምት ሳያሰራ 45 ሚሊየን ብር ይሆናል ተብሎ ይታሰባል በሚል ውስን ጨረታን ለማስፈቀድ የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለስልጣንን በደብዳቤ መጠየቃቸው እና ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ለደብዳቤው ምላሽ ከሰጣቸው በኋላ የመሃንዲስ ግምት 46,075,174.33 ብር ማሰራታቸው፣ የኢንስቲትዩቱ የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 008/2013 ለውስን ጨረታ የግንባታ ሥራ ግዥ የተቀመጠው 18 ሚሊዮን ሆኖ እያለ ተጫራቹ በ45,599,766.65 ብር በግዥ ኮሚቴ አሸናፊ ተብሎ መለየቱ፣ ኢንስቲትዩቱ ተቋራጮችን ለመጋበዝ ከተማ እና መሰረተ ልማት ሚኒስቴርን መጠየቅ ሲገባው ባለበት ክፍለ ከተማ እና ለአ/አ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የተቋራጭ ዝርዝር በደብዳቤ መጠየቁ፣ ሳበርኮን ኢንጅነሪግን የኢንስቲትዩቱ ግቢ አጥር ሥራ መጀመሪያ ከተዋዋለበት በ3,244,391.96 ብር ለመስራት ከተዋዋለ በኋላ የአስፓልት መንገድ እንዲሰፋ የከተማ አስተዳደሩ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ክፍያው ወደ 10,261,574.21 ብር በማሳደግ ለተቋራጩ እንዲከፈለው በቀን 05/13/2016 በቁጥር 02/02/74/16 ለበላይ አመራር በተፃፈ ደብዳቤ የተፈጸመ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ሆኖም ዝርዝር የክፍያ ሰነድ ላይ የተሰሩ ስራዎች አለመቀመጥ እንደክፍተት ታይቷል፣ እንዲሁም ከዚህ በፊት የቢሾፍቱ 72 የሥልጠና የመኝታ ክፍሎችን የእድሳት ሥራ በሰራበት ወቅት ስራውን በተሰጠው ጊዜ ባለማጠናቀቁ ኢንስቲዩትቱ ማግኘት ያለበትን 18 ሚሊዮን ብር ያሳጣ መሆኑን ለመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ከተፃፈ ደብዳቤ ላይ የተመላከተ ቢሆንም በዚህ ውስን ጨረታ በድጋሚ እንዲወዳደር መደረጉ፣ ኢንስቲትዩቱ የሳበርኮን ኢንጅነሪንግ የአፈፃፀም ደረጃው በገለልተኛ አካል ሳይረጋገጥ የተሻለ አፈፃፀም አለው በማለት በውስን ጨረታው ላይ ኢንዲሳተፍ መደረጉ፣ የውስን ጨረታ ግዥው በኢንስቲትዩቱ በግዥ አጽዳቂ ኮሚቴዉ ዉድቅ የተደረገ ቢሆንም ያለምንም ውሳኔ ለግለሰቡ እንዲሰጥ መደረጉ፣ የቴክኒክ ምዘና የፍላጎት መግለጫ እና የመሃንዲስ ግምት በአንድ ሰው መደረጉ፣ ውስን ጨረታ ለማውጣት ከመንግሥት ንብረት አስተዳደርና ግዥ ባለስልጣን ሚያዚያ 03/2017 ዓ.ም በደብዳቤ ከተጠየቀበት ጥቆማው ለኮሚሽኑ እስከ ደረሰበት ሐምሌ/2017 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ግዥው ግልፅ ጨረታ ለማካሄድ የነበረው ጊዜ በቂ መሆኑ፣ ኢንስትቲዩቱ ውስን ጨረታ ለማስፈቀድ ለመንግሥት ግዥ እና ንብረት ባለሥልጣን ደብዳቤ ከመፃፉ በፊት የግዥ ኮሚቴው የተወያየበት ቃለ ጉባኤ አለመኖር እና ውስን ጨረታው ከተፈቀደ በኋላ የግዥ ኮሚቴው ተጫራቾችን በውስን ጨረታ ማሳተፍ የሚቻልበትን ሁኔታ ስለመወሰን በሚል ለይስሙላ በሚመስል መልኩ ቃለ ጉባኤ በመያዝ መወያየታቸው የሚሉት ናቸው።

### የጥናቱ ምክረ ሃሳብ

የጥናት ቡድኑ ከላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦችና ግኝቶች በጥልቀት በማየት የውስን ጨረታ ግዥው የመንግስት ንብረትና ግዥ ባለስልጣን የግዥ አዋጅ እና መመሪያን በመከተል ተግባራዊ ቢደረግ፣ ኢንስቲትዩቱ በእቅድ መመራት ቢችል፣ በምክንያታዊ የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ መመራት፣ ኢንስቲትዩቱ ትልልቅ ግንባታና ሌሎች ተግባራትን ለማከናወን የበጀት እቅድ መያዝ፣ የግንባታ ግዥና የመሀንዲስ ዋጋ ግምት የሚሰራ ብቃት ያለው ባለሙያ በቋሚነት ቀጥሮ ማሰራትና ለጥቅም ግጭት የሚያጋልጡ ስራዎችን ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላትን ብሎም ማኔጅመንቱን በማሳተፍ በመገምገም ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ ቢቻል የሚል ምክረ ሃሳብ አስቀምጧል። ውል የተያዘባቸው የግንባታ ስራ ለምሳሌ የግቢው የአጥር ስራ ሲኖርና ሌላ ተጨማሪ ስራ ሲካተት በተቻለ መጠን ተጨማሪ ስራው መመሪያ ከሚፈቅደው በላይ ከሆነ ራሱን የቻለ የግዥ እቅድ ቢሆን እንዲሁም ለዋናው የኢንስቲትዩቱ አጥር መጀመሪያ ከተዋዋሉበት 3,000,000.00 ወደ 10,261,574.21 የተከፈለው የተጨማሪ ስራ ክፍያ በጥቅሉ የተቀመጠ ስለሆነ ዝርዝር ስራዎች ስለመሰራታቸውና ክፍያው ስለመፈጸሙ በውስጥ ኦዲት ቢታይ ሲል ኮሚሽኑ ምክረ -ሀሳብ አቅርቧል።

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

“የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ተልዕኮውን ለመወጣት በየጊዜው የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ግንባር ቀደም ሚና እየተጫወተ ይገኛል:: ከእነዚህም መድረኮች መካከል በየሁለት ሳምንቱ ለንባብ የሚበቃው ዲጂታል ጋዜጣችን አንዱና ዋነኛው ነው:: ጋዜጣችን ከያዛቸው አበይት ዓምዶች መካከል ‘ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር’ የሚለው ይገኝበታል:: በዚሁ መሠረት በዚህ እትማችን ለህብረተሰቡ ትምህርት ይሰጣሉ ብለን ያመንንባቸውንና በሙስና ወንጀል የተሳተፉ ግለሰቦችን ጉዳይ አስመልክቶ የተዘጋጀውን ዝርዝር መረጃ ለአንባቢዎቻችን አቅርበናል::”

የሙስና ወንጀል የፈፀሙ ግለሰቦች በፅኑ እስራት እንዲቀጡና የመዘበሩትን የህዝብና የመንግስት ሀብት እንዲመልሱ ውሳኔ ተላለፈባቸው::

ተከሳሾች 1ኛ/ ትዕዛዙ ሳካ 2ኛ/ አይናለም አጃቦ 3ኛ/ ብርቱካን ዳሎ 4ኛ/ እየሩሳሌም ኦሎሎ 5ኛ/ ቤዛዊት ግዴቦ ሲሆኑ:-

1ኛ ተከሳሽ በሶዶ ከተማ ዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ የሂሳብ ባለሙያ ሆኖ ተቀጥሮ በሰራባቸዉ ጊዜያቶች ከቀን 27/5/2016ዓ.ም እስከ 14/10/2016ዓ.ም ድረስ ያለዉ የዳቦ ሽያጭ ገንዘብ በአግባቡ ገቢ ስለመደረጉ ኦዲት ሲደረግ ብር 898,659/ስምንት መቶ ዘጠና ስምንት ሺ ስድስት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ በፋብሪካዉ ሂሳብ ገቢ የተደረገ በማስመሰል የተዘጋጀ ሐሰተኛ የባንክ ደረሰኝ በመጠቀም የፋብሪካዉን ገንዘብ ለግል ጥቅም ያዋለ በመሆኑ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት አስበዉ በፈጸመዉ ሐሰተኛ ሰነድ በመገልገል የሙስና ወንጀል መከሰሱን መዝገቡ ያሳያል ::

በተጨማሪም 1ኛ ተከሳሽ በሶዶ ከተማ ዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ የሂሳብ ባለሙያ ሆኖ ተቀጥሮ በሰራባቸዉ ጊዜያቶች ከቀን 27/5/2016 ዓ.ም እስከ 14/10/2016ዓ.ም ድረስ ያለዉ የዳቦ ሽያጭ ገንዘብ በአግባቡ ገቢ ስለመደረጉ ኦዲት ሲደረግ ወጪ ካደረገዉ የሽያጭ ገቢ ደረሰኝ መካከል የንምራ ቁጥራቸዉ 000528 እና 001380 የሆኑትን ሁለት ዋናዉን/ ኦሪጅናል ደረሰኞች ነቅሎ ያጠፋ በመሆኑ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት አስበዉ በፈጸመዉ በማጥፋት የሙስና ወንጀል ተከሷል።

ከ2ኛ እስከ 4ኛ ድረስ በተጠቀሱት ተከሳሾች ላይ የኢ/ፌ/ዲ/ሪ ወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 15/2 ላይ የተደነገገዉን በመተላለፍ የተከሰሱ ሲሆን 2ኛ_4ኛ ድረስ ያሉ ተከሳሾች በሶዶ ከተማ ዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ ሽያጭ ባለሙያ ሆነው ተቀጥረው በሰሩባቸዉ ጊዜያቶች ከቀን 27/5/2016 ዓ.ም እስከ 14/10/2016ዓ.ም ድረስ ያለዉ የዳቦ ሽያጭ ገንዘብ በአግባቡ ገቢ ስለመደረጉ ኦዲት ሲደረግ በ2ኛ ተከሳሽ ላይ ብር 376,885/ሶስት መቶ ሰባ ስድስት ሺ ስምንት መቶ ሰማንያ አምስት፣ በ3ኛ ተከሳሽ ላይ ብር 334,120/ሶስት መቶ ሰላሳ አራት ሺ አንድ መቶ ሃያ እና በ4ኛ ተከሳሽ ላይ ብር 271,160/ሁለት መቶ ሰባ አንድ ሺ አንድ መቶ ስልሳ ጉድለት የተገኘ በመሆኑ ሁሉም ተከሳሾች ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት አስበዉ በፈጸሙት በስራ ተግባር በሚፈጸም መዉሰድ እና መሰወር የሙስና ወንጀል ተከሰዋል፡፡

5ኛ ተከሳሽ በሶዶ ከተማ ዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ ሽያጭ ባለሙያ ሆና ተቀጥራ በሰራችባቸዉ ጊዜያቶች ከቀን 27/5/2016 ዓ.ም እስከ 14/10/2016ዓ.ም ድረስ ያለዉ የዳቦ ሽያጭ ገንዘብ በአግባቡ ገቢ ስለመደረጉ ኦዲት ሲደረግ በ5ኛ ተከሳሽ ላይ ብር 40,810/አርባ ሺ ስምንት መቶ አሥር ጉድለት የተገኘ በመሆኑ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት አስባ በፈጸመችዉ በስራ ተግባር በሚፈጸም መዉሰድ እና መሰወር የሙስና ወንጀል መከሰሷን ከመዛግብት መመልከት ተችሏል፡፡

ግራ ቀኙን ሲያከራክር የቆየው የወላይታ ሶዶ ከተማ አስተዳደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዐ/ህግ ያቀረበውን ክስ በሰውና በሰነድ ማስረጃ ያስረዳውን 1ኛ ተከሳሽ ያላስተባበለ ስለሆነ በዋለው ችሎት ፍ/ቤቱ 1ኛ ተከሳሽን ጥፋተኛ በማድረግ 1ኛ ተከሳሽ በ6 ዓመት ከ9 ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጣና የተመዘበረውን 898,659 ብር ከሕጋዊ ወለድ ጋር ለመንግሥት እንዲመልስ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

2ኛ እስከ 5ኛ ድረስ ያሉ ተከሳሾች በተመለከተ የጥፋተኝነት ውሳኔ በማሳለፍ ተከሳሾች የወንጀል ሪከርድ የሌለባቸው፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን ከህጻናት ጥቅም አንጻር ግምት ውስጥ በማስገባት ተከስሾች እያንዳንዳቸው በአንድ ዓመት ቀላል እስራት እንዲቀጡ በመወሰን ቅጣቱ በሁለት አመት ፈተና ጊዜ ታግዶ እንዲቆይ ውሳኔ አሳልፏል ::

በሌላ መረጃ የሲዳማ ክልል ሰላምና ጸጥታ ቢሮ የቀድሞ ኃላፊ አቶ አለማየሁ ጢሞቴዎስ ጨምሮ ሌሎች የቢሮው ኃላፊዎች የጽኑ እስራት ውሳኔ ተላልፎባቸዋል፡፡

የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀድሞው የሲዳማ ክልል ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊ አቶ አለማየሁ ጢሞቴዎስ እና የፖሊስ ኮሚሽነር ሽመልስ ቶማስ ላይ የክልሉ ፍትህ ቢሮ ከሳሽነት በቀረቡ ክሶች ላይ የጽኑ እስራት ውሳኔ አስተላልፏል፡፡

ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የሰውና የሰነድ ማስረጃ በማመሳከር ተከሳሾቹን ጥፋተኛ ያላቸው ስልጣንን አላግባብ በመገልገል የሲዳማ ነፃነት ሠራዊት የተባለ ታጣቂ ቡድን በማደራጀትና ተደራራቢ የሰብዓዊ መብት ጥሰት መፈጸማቸውን በማረጋገጥ ነው፡፡

በዚህም መሰረት ፍርድ ቤቱ በዋለው ችሎት 1ኛ ተከሳሽ አቶ አለማየሁ ጢሞቴስን በ10 ዓመት ከአምስት ወር ጽኑ እስራት እና የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጡ ተወስኗል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ አቶ ሽመልስ ቶማስን በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እና የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጡ ውሳኔ መተላለፉን አረጋግጧል፡፡

# መልካም ዜጋ

## 300 ሺህ ብር ለባለቤቱ የመለሱት ግለሰብ ምስጋና ተቸራቸው




በአማራ ክልል ደሴ ከተማ ነዋሪ የሆኑት አቶ ኡመር እሸቱ በስህተት ወደ ባንክ ሂሳባቸው ገቢ የተደረገን 300 ሺህ (ሦስት መቶ ሺህ) ብር ለባለቤቱ በመመለስ የታማኝነትና የቅንነት አርዓያነትን አሳይተዋል፡፡

በስህተት 300 ሺህ ብር በባንክ አካውንታቸው የገባላቸው አቶ ኡመር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መናፈሻ ቅርንጫፍ በአካል በመገኘት ለገንዘቡ ባለቤት ለአቶ ሁሴን አህመድ ገቢ እንዲሆን ማድረጋቸው ተገልጿል፡፡ አቶ ኡመር ያሳዩት ተግባር የታማኝነትና ቅንነት እሴትን የሚያጎላና ለሌሎችም መልካም አርዓያ በመሆኑ ምስጋናና አክብሮት ይገባቸዋል ተብሏል፡፡

አቶ ኡመር እሸቱ ያሳዩት በጎ ተግባር ተራ የገንዘብ ዝውውር መመለስ ብቻ ሳይሆን፣ የአንድን መልካም ዜጋ ሁለንተናዊ ምስል የሚያንፀባርቅ ህያው ማሳያ ነው፡፡ በዲጂታል ዘመን እና በኢኮኖሚያዊ ፈተናዎች ውስጥ መልካም ዜግነት በባህሪ እና በድርጊት እንዴት እንደሚገለጽ የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች አንስቶ ማየት ይቻላል፡-

ህሊናዊ ታማኝነት እና የስነ-ምግባር ልዕልና መልካም ዜግነት የሚጀምረው ማንም በማያየን ወይም ህጋዊ ተጠያቂነት በማይኖርበት አጋጣሚ እንኳን ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ ከሚወሰን የውስጥ ስነ-ምግባር ነው፡፡ አቶ ኡመር በስህተት የገባውን 300 ሺህ ብር በራሳቸው ሂሳብ ውስጥ እያለ መመለሳቸው፣ በህግ የመጠየቅ ስጋት ብቻ ሳይሆን የህሊና ዳኝነት እና የግል ስነ-ምግባር እንደመራቸው ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ ለአንድ ሀገር ግንባታ ዋናው የማዕዘን ድንጋይ የሆነውን “የታማኝነት እሴት” ያጠናክራል፡፡

የሙስና እና የብልሹ አሰራር መከላከል መሰረት ሙስና እና ብልሹ አሰራር የሚስፋፋት የሌላውን ድካምና ንብረት ያለአግባብ የመውሰድ አመለካከት ሲሰፍን ነው፡፡ መልካም ዜጋ ደግሞ ያልደከመበትን እና የራሱ ያልሆነን ንብረት የመጠበቅ እና የመመለስ ኃላፊነት አለበት፡፡ የዜጎች የግል ታማኝነት ሲጎለብት ተቋማዊ አሰራር ይበልጥ ይጠናከራል፤ ህብረተሰቡም ከብልሹ አሰራር የጸዳ ንቁ ማህበረሰብ ለመገንባት የሚያደርገውን ጉዞ ያፋጥነዋል፡፡

ማህበራዊ መተማመንን ማጎልበት በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ልማት እና ሰላም የሚረጋገጠው በሰዎች መካከል ጠንካራ “ማህበራዊ መተማመን”ሲኖር ነው፡፡

ለቀጣዩ ትውልድ አርአያነት መልካም ዜግነት በቃላት የሚነገር ሳይሆን በተግባር የሚታይ ትምህርት ነው፡፡ አቶ ኡመር ለንግዱ ማህበረሰብም ሆነ ለወጣቱ ትውልድ ትልቅ ተግባራዊ ትምህርት አስተላልፈዋል፡፡ ንግድና ሀብት የሚባረከውና ዘላቂ የሚሆነው በታማኝነት እና በቅንነት ላይ ሲመሰረት እንደሆነ የሚያሳይ ትልቅ ማሳያ ነው፡፡

መልካም ዜግነት የሚለካው በቃላት ሳይሆን በተግባር በሚታይ ታማኝነትና ህሊናዊ ሚዛን ነው፡፡ ያልደከሙበትንና የራሳቸውን ያልሆነን ንብረት ለትክክለኛው ባለቤት መመለስ የግል ስነ-ምግባር ልዕልናን ብቻ ሳይሆን፣ በማህበረሰቡ ዘንድ መተማመንን የሚያጠናክርና ሙስናን የመከላከል ባህልን የሚያጎለብት ትልቅ በጎ አርዓያነት ነው፡፡



# ኪነ-ጥበብ

## ዱባ እንደመሪው ነው




አባቶቻችን ተረትና ምሳሌ አነጋገር እንዲሁ በአጋጣሚ ምላስ ላይ የወደቀ የቃላት ድርድር አይደለም:: ከዘመናት ተሞክሮ፣ ከተፈጥሮ ህግጋትና ማህበራዊ ህይወት ምሥጢር ተጨልፎ ለትውልድ የተላለፈ የህይወት ፍልስፍና እንጂ::

በአገራችን አባባል «ዱባ እንደመሪው ነው» የሚል ብሂል አለ:: ነገሩን ቀረብ ብሎ ላስተዋለው የዱባ ተክል ባሕሪው ድንቅ ነው:: የዱባው ግንድ (መሪው) አቅጣጫውን ይዞ ወዴት እንደሚንቀሳቀስና የት እንደሚያርፍ ሲወስን ፍሬው ደግሞ ያንኑ መሪ ተከትሎ እዚያው ቦታ ላይ ያብባል፣ ያፈራል:: መሪው አጥር ላይ ካለፈ ፍሬው አጥር ያቋርጣል፣ መሪው ገደል ከከተተው ፍሬው ገደል ይገባል:: ይህ የጓሮ ጥበብ ታዲያ ከአፈርና ከቅጠል አልፎ በዘመናዊ ተቋማት በማህበራዊ ህይወትና በሀገራዊ ተቋማት አመራር ደረጃ በትክክል የሚሰራ የነጠረ እውነታ ነው:: በተለይም በስነ-ምግባር ግንባታና በሙስና ትግል ዙሪያ ገላጭ ምሳሌ ሊሆን ይችላል:: አብዛኛውን ጊዜ በየተቋማቱ የምናየው የባህሪ ብልሹነትና ሙስና ከስር የሚበቅል ብቻ ሳይሆን ከላይ የሚወርድም «ተላላፊ በሽታ» ነው:: የአንድ ተቋም ወይም የማህበረሰብ የስነ-ምግባር አቅጣጫ የሚወሰነው ከላይ ባለው አመራር የዕለት ተዕለት አቋም ነው::

መሪው ለህግና ለስነ-ምግባር የሚገዛ፣ ግልጸኝነትንና ተጠያቂነትን የሚያስቀድም ከሆነ፤ የበታች ሰራተኛው ያንን ፈለግ ተከትሎ ቀናውን መንገድ ለመያዝ አይቸገርም:: በአንጻሩ መሪው ለአቋራጭ ብልጽግና፣ ለጥቅም ግጭት፣ ለታይታና ለሙስና በሩን ከከፈተ ግን ተቋሙ ሙሉ በሙሉ በዚሁ የስነ-ምግባር ብልሹነት መረብ ውስጥ መውደቁ አይቀሬ ነው:: መሪው «ትንሽ ጉቦ መቀበልን» ወይም «ጥቅም መጋራትን» እንደ መደበኛ አሰራር ካየው የበታች ሰራተኞች ደግሞ ይበልጥ ደፍረው ስርዓት አልበኝነትን ይለማመዱታል:: ስለዚህም የስነ-ምግባር መበላሸት የሚጀምረው በግለሰብ ሰራተኞች ዘንድ ብቻ ሳይሆን በአመራሩ የዕሴት ውድቀትም ነው::

እውነተኛ አርአያ መሪ ማለት በቃላት የሚያዝዝ፣ በመድረክ መመሪያዎችን የሚናገር ሳይሆን በተግባሩ መንገድ የሚያሳይ ነው:: የዱባው ግንድ የት እንደሚያርፍ ፍሬው እንደሚያየው ሁሉ ሰራተኛውም የመሪውን እውነተኛ ጠባይና ውሳኔ በቅርብ ይከታተላል:: የተቋም የስነ-ምግባር ባህል የሚገነባው በሚወጡ ደንቦች ግድግዳ ላይ በሚሰቀሉ መፈክሮች ብቻ ሳይሆን በመሪዎች ታማኝነትና ቅንነት ነው:: መሪው ራሱን ከተጠያቂነት በላይ ካደረገ ስር ያለው አሰራር በሙሉ ፈራርሶ ለሙስና የተመቸ ሁኔታ ይፈጠራል::

በየተቋማቱ የሙስናና የስነ-ምግባር ብልሹነትን ለማስወገድ የሚደረገው ትግል ዘላቂ ውጤት ሊያመጣ የሚችለው ፍሬውን («ዱባውን» ወይም የበታች አሰራሩን) ብቻ በመመልከትና በመቅጣት ሳይሆን መሰረቱን («መሪውን» ወይም የላይኛውን አመራርና አቅጣጫ) በመፈተሽና በማስተካከል ነው::

የጥንቶቹ አባቶቻችን በምሳሌያቸው እንዳስገነዘቡን ሁሉ የመሪው መስመር ከተቃና ፍሬውም የበሰለ ጤናማና ለሁሉም የሚጠቅም ይሆናል:: የተቋማችንም ሆነ የሀገራችን ብልጽግና የሚጀምረው ከመሪዎቻችን የስነ-ምግባር ጥራት ነው::